# የቪዲዮ ጥናት መመሪያ
## እንኳን ወደ ትውልድ መሬቶቻችን/ሀገራችን በደህና መጡ

## አጠቃላይ እይታ

ወደ ካናዳ እንኳን በደህና መጡ ቪዲዮው ስለ ተወላጆች እሴቶች እና አመለካከቶች ሰፊ ሃብትን ለማስተዋወቅ ይሞክራል፡ ይህም ይህችን ሀገር የመሰረቱትን በርካታ ውስብስብ ታሪካዊ ክስተቶች እና በአገሬው ተወላጅ እና ተወላጅ ባልሆኑ ህዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጉላት ነው።

ቪዲዮውን ከተመለከቱ በኋላ፣ ስለ ካናዳ ተወላጆች የበለጠ ለመማር እንዲቀጥሉ ተስፋ እናደርጋለን። ይህ አብሮ የሚሄድ የቪዲዮ ጥናት መመሪያ ስለ ካናዳ ተወላጆች ያለዎትን ግንዛቤ ለመጨመር ተጨማሪ መረጃ፣ የተጠቆሙ አገናኞች (links) እና ስነ-ቃላት (terminology) ይሰጣል። ለተጨማሪ ትምህርት ይህንን መመሪያ እንደ መነሻ እንደሚጠቀሙበት ተስፋ እናደርጋለን።

ካናዳ የአገሬው ተወላጆችን እንዴት ትገልጸዋለች? የካናዳ ሕገ-መንግሥት ሕግ ክፍል 35 (2)፣ 1982 የድሮ የመሬቱ ነዋሪ (Aboriginal) ሕዝቦች “ህንድ፣ ኢኑይት (Inuit) እና ሜቲስ (Métis) የካናዳ ሕዝቦችን እንደሚያካትቱ ይገልጻል።

“ህንድ” የሚለው ቃል እንደ አጸያፊ የቅኝ ግዛት ቃል ይቆጠራል። የካናዳ ተወላጆችን በሚወያዩበት ጊዜ **ተወላጅ (Indigenous)** የሚለው ቃል ከአቦርጂናል የበለጠ ተመራጭ ነው።

**የመጀመሪያ ብሔሮች (First Nations)** የሚለው ቃል ተወላጆች ለሆኑና እና እንደ ኢኑይት ወይም ሜቲስ ብለው የማይታወቁ ሰዎችን ለማመልከት የሚያገለግል ቃል ነው።

- *en.wikipedia.org/wiki/Indigenous_peoples_in_Canada*

**ኢኑይት (Inuit)** በካናዳ፣ ግሪንላንድ እና አላስካ አርክቲክ ክልሎች ውስጥ ባሉ 53 ማህበረሰቦች ውስጥ የሚኖሩ የተወላጆች ስብስብ ናቸው። ከታሪክ አንጻር ኢኑይት (Inuit) “ኤስኪሞስ” (“Eskimos”) ተብለው ይጠሩ ነበር፣ ነገር ግን ይህ ቃል አክባሪ አይደለም፣ እና ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።

- *en.wikipedia.org/w/Inuit*

**ሜቲስ (Métis)** “መቀላቀል” ከሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የመጣ ነው። እነሱ ዘሮቻቸውን ከመጀመሪያ ብሔሮች (First Nations) እና አውሮፓውያን ቅይጥ የዘር ግንድ የተገኘ የተለየ ተወላጅ ቡድን ናቸው። ዘሮቻቸው “ዲቃላ/ክልስ” ተብለው ይጠሩ ነበር፣ አሁን ኣይጠሩበትም እንደ አጸያፊም ይቆጠራል።

- *en.wikipedia.org/wiki/M%C3%A9tis_in_Canada*

## በቪዲዮው ውስጥ

እ.ኤ.አ. በ 2016 በካናዳ ውስጥ 1,673,785 ተወላጆች (Indigenous) ነበሩ ፣ እሱም ከጠቅላላው ህዝብ 4.9% ይወክላል። ዛሬ፣ በካናዳ ውስጥ ወደ 634 ኣከባቢ የተለያዩ ከመጀመሪያ ብሔሮች (First Nations) እና በግምት 60 የተለያዩ የቋንቋ ቡድኖች፣ በመላው ካናዳ፣ በባህላዊ ግዛቶች እና በከተማ ማዕከሎች ይኖራሉ።

- *en.wikipedia.org/wiki/First_Nations*

በቪዲዮው ላይ፣ ከመላው ካናዳ በመጡ ስድስት የአገሬው ተወላጅ ተወካዮች አስተዋውቀው እና አቀባበል አድርገውልዎታል። ስለእነዚህ ተወላጆች ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አገናኞች (link) ማግኘት ይችላሉ፥

**ግዋዪ - GWAYEE (የብሪቲሽ ኮሎምብያ – የመጀመሪያ ብሔሮች - FIRST NATIONS)**

- *kingcome.ca*
- *youtube.com/watch?v=0ClB0OxJkiY*

**ኢኑቪክ (ሰሜናዊ ምዕራብ ግዛቶች – ኢኑይት)**

- *inuvik.ca/en/index.asp*
- *en.wikipedia.org/wiki/Indigenous_peoples_in_Northern_Canada*

**ፔንቲክተን - PENTICTON (የብሪቲሽ ኮሎምብያ – የመጀመሪያ ብሔሮች - FIRST NATIONS**

- *syilx.org/about-us/syilx-nation*
- *pib.ca*

**ስድስት ብሔሮች (ኦንታርዮ)**

- *sndevcorp.ca/history-of-six-nations*
- *en.wikipedia.org/wiki/Six_Nations_of_the_Grand_River*

### ዩናማ’ኪ - UNAMA’KI (ኬፕ ብሬተን - CAPE BRETON፣ ኖቫ ስኮሽያ)

- *cbu.ca/indigenous-affairs/mikmaq-resource-centre/mikmaq-resource-guide/historical-overview*

### ኢለኣላ ክሮስ-ÎLE-A-LA CROSSE (የሳስካችዋን ሜቲስ)

- *en.wikipedia.org/wiki/%C3%8Ele-%C3%A0-la-Crosse*

ይህን ቪዲዮ በካናዳ ውስጥ ከተመለከቱ፣ በማህበረሰብዎ ወይም በክልልዎ ስላሉት የመጀመሪያ ብሔሮች የበለጠ ይወቁ። ከተማዎ የማን ተወላጅ ግዛት እንደሆነች ለማየት በጉግል (Google) ፍለጋ መጀመር እና ሌሎች ማገናኛዎችን (links) መመልከት ይችላሉ።

የአገሬው ተወላጆች የተለየ እሴት እና የቃል ወጎች አሏቸው። ታሪኮች እና የኣፍ ታሪኮች የሀገር-በቀል ማንነትን እና ባህልን ለመጠበቅ ወሳኝ ናቸው። ብዙውን ጊዜ የቃል ታሪክን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማስታወስ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ሚና ነው። የአገሬው ተወላጆች እሴቶችን እና ታሪኮችን ከትውልድ ወደ ትውልድ በአፍ በመተረክ ያስተላልፋሉ። የአገሬው ተወላጆች ባህሎች የኣፍ ታሪኮችን እና ታሪኮችን በምሳሌያዊ (symbolic) ነገሮች እና ስእላዊ ቋንቋ እንደ የተቀረጹ የምስል (totem) ምሰሶዎች እና የቤት ውስጥ ምሰሶዎች ያወራሉ።

እያንዳንዱ የአገሬው ተወላጅ ባህል፣ ማህበረሰብ እና ቤተሰብ እንኳን የራሱ ታሪካዊ እና ባህላዊ ታሪኮች፣ ዘፈኖች ወይም ጭፈራዎች አሉት። የተለያዩ ባህሎች ስለ ባለቤትነት የተለያዩ ህጎች አሏቸው። አንዳንድ ዘፈኖች፣ ስሞች፣ ምልክቶች ወይም ውዝዋዜዎች የአንዳንድ ሰዎች ወይም ቤተሰቦች ናቸው እና ያለፈቃድ ጥቅም ላይ ሊውሉ፣ ሊደገሙ፣ ሊጨፈሩ ወይም ሊዘፈኑ አይችሉም።

## ቁልፍ ክስተቶች

በካናዳ ተወላጆች እና ተወላጅ ያልሆኑ ህዝቦች መካከል ያለው ታሪካዊ ግንኙነት ውስብስብ እና በቅኝ ግዛት፣ በታሪካዊ ክስተቶች፣ በህጎች እና በዘረኝነት አመለካከቶች ላይ ተጽእኖ ያደረበት ነው። እነዚህ ክንውኖች ዛሬም በአገሬው ተወላጆች ዘንድ የሚሰማቸውን ወቅታዊ ጉዳዮችን ቀርፀዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ በካናዳ ውስጥ ያለፈውን ታሪካዊ ስህተቶች ለማሻሻል እና ለመፍታት የተለያዩ መነሳሳቶች አሉ።

ይህ የጥናት መመሪያው የመጨረሻ ክፍል በቪዲዮው ላይ የደመቁ ቁልፍ ታሪካዊ ክንውኖች ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት ይሞክራል።

### ቅኝ ግዛት

- *en.wikipedia.org/wiki/History_of_Canada*

አውሮፓውያን ከመምጣታቸው በፊት ሰሜን አሜሪካ በተለየ በራሳቸው ባህል፣ ቋንቋ እና የእውቀት መንገድ በሚኖሩና በሚዳብሩ ተወላጆች ተይዛ ነበረች። የአገሬው ተወላጆች አሁን ካናዳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ከ10,000 ዓመታት በላይ ኖረዋል።

ብሪቲሽ እና ፈረንሣይ (የካናዳ ሁለቱ መስራች ሀገር ናቸው የሚባሉ) ሀብታም የጥሬ ዕቃ ምንጭ አድርገው ለሚቆጥሩት ሰሜን አሜሪካን ለመቆጣጠር ሲዋጉ ነበር። አውሮፓውያን ሰሜን አሜሪካ ሲደርሱ “ባለቤት የሌለው መሬት” አድርገው ይመለከቱት ነበር። አውሮፓውያን የራሳቸውን ባህላዊ እሴቶች፣ ሃይማኖቶች፣ ህጎች ጫና ኣድርገው/ኣስገድደው ለእነርሱ በሚጠቅም መንገድ ፖሊሲዎች አውጥተዋል፡ ለአንዳንዶቹ የአገሬው ተወላጆች “ሰዎች” ናቸው ብለው አያምኑም ነበር።

በውጤቱም የአውሮፓ እሴቶች እና እምነቶች በካናዳ ተቋማት እና ፖሊሲዎች ስርአታዊ እና ተቋማዊ መድልዎ እና አድልዎ ውስጥ ገብተዋል። ዛሬ አብዛኛው ስራ ያለፈውን ስህተት ማስተካከል እና መድልዎ እና ጭፍን ጥላቻ የሚያስከትለውን መዘዝ ማሸነፍ ነው።

### የህንድ ህግ, 1876

- *en.wikipedia.org/wiki/Indian_Act*

የህንድ ህግ ላገሬው ተወላጅ የተወሰነ መሬት (Reserves) እና ባንዶች (Bands) እንዴት እንደሚሰሩ የሚያመለክት እና ማን እንደ “ህንድ” እውቅና ያለው መሆኑን የሚገልጽ የፌዴራል ህግ ነው። የህንድ ህግ የመጀመሪያው ብሔሮች ሰዎችን በተቻለ ፍጥነት ከአውሮፓ ማህበረሰብ ጋር ለማዋሃድ ሌላ ሙከራ ነበር። ሕጉ ኣንድ ‘ህንድ’ ያገኘው ወይም የጠፋበት ሁኔታ፣ የሴቶች ህጋዊ ሁኔታ፣ የባለቤትነት መብት ወዘተ የመሳሰሉ ብዙ የተለያዩ ገጽታዎችን ያጠቃልላል። የህንድ ህግ ዛሬም ገና በስራ ላይ ያለ ሲሆን አሁንም ለአገሬው ተወላጆች ፈታኝ የሆነ የህግ አካል ነው።

**የተወሰኑ መሬቶች (Reserves)፡** በአውሮፓውያን መምጣትና መስፈር፣ የመጀመሪያ ብሔሮች ሰዎች እና አውሮፓውያን እነዚህን መሬቶች እና ሃብቶች ማን ይቆጣጠራል በሚል ግጭት ውስጥ ገቡ፣ እናም የመጀመሪያ ብሔሮች ህዝቦች የተወሰኑ መሬቶች (Reserves) በሚባሉ ትናንሽ መሬቶች ላይ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ብዙ የመጀመሪያ ብሔሮች አሁንም መንግሥት በሚቆጣጠራቸው አነስተኛ የተወሰኑ መሬቶች (Reserves) ላይ መኖር ቀጠሉ። ይህ በአገሬው ተወላጅ ህዝቦች እና በመንግስት መካከል ያለው የብዙ ግጭቶች መንስኤ ነው

### የመኖሪያ ትምህርት ቤቶች (RESIDENTIAL SCHOOLS)

- *en.wikipedia.org/wiki/Canadian_Indian_residential_school_system*

ከህንዱ ሕግ በጣም ከሚያስጨንቁ ቅርሶች አንዱ በመኖሪያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመገኘት ግዴታ ነበር። በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ የተደገፉ እና በአብያተ ክርስትያናት የሚተዳደሩ 140 የህንድ መኖሪያ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ከ150,000 የሚበልጡ የአገሬው ተወላጆች ልጆች በእነርሱ ላይ እንዲገኙ ተገደዋል። መንግስት የአገሬው ተወላጆችን ከዩሮ-ካናዳዊ (Euro-Canadian) ማህበረሰብ ጋር ለማዋሃድ ፈልጎ ነበር።

የአገሬው ተወላጆች ልጆች ከወላጆቻቸው እና ከቤተሰቦቻቸው ተወስደው ሁሉንም ቋንቋቸውን፣ መንፈሳዊ እምነቶቻቸውን እና ባህላዊ ልማዶቻቸውን ለመተው ተገደዱ። በሰኔ 11ኛ 2008 የካናዳ መንግስት ከመኖሪያ ትምህርት ቤት የተረፉ ሰዎችን መደበኛ ይቅርታ ጠይቀ። በጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበውን የይቅርታ ግልባጭ በሚከተለው አገናኝ (link) ያገኙታል።

- *rcaanc-cirnac.gc.ca/eng/1100100015644/1571589171655*

### የተገደሉ እና የጠፉ ሴቶች እና ልጃገረዶች

- *mmiwg-ffada.ca/final-report*

በመስከረም 2016፣ የካናዳ መንግስት በተገደሉ እና በጠፉ የአገሬው ተወላጅ ሴቶች እና ልጃገረዶች (MMIWG) ላይ ብሔራዊ ምርመራን ጀምሯል። MMIWG የሚያመለክተው በ1980 እና 2012 መካከል በጠፉ እና በተገደሉ የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ምክንያት የሰብአዊ መብት ቀውስን ነው። የአገሬው ተወላጆች የሴቶች ቡድኖች የጠፉ እና የተገደሉትን ቁጥር ከ4,000 በላይ መሆኑን በሰንድ ያስቀምጣሉ። የግንዛቤ መጨመር ለአገሬው ተወላጅ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች ከፍተኛ ድጋፍ አስገኝቷል እናም ሰዎችን ፍትህን የመፈለግ የጋራ ግብ አንድ ላይ አምጥቷቸዋል።

## የተሻለ መጻኢ መገንባት

### የእውነት እና እርቅ ኮሚሽን (TRC)

- *cbc.ca/news/politics/truth-and-reconciliation-94-calls-toaction-1.3362258*

የፌደራል መንግስት የመኖሪያ ትምህርት ቤቶችን ውርስ ለመመርመር የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽንን (TRC) በ2008 አቋቋመ። የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽንን (TRC) ሥልጣን በካናዳ ከመኖሪያ ትምህርት ቤት ስርዓት የተረፉትን የ80,000 ዎቹ ልምዶች (experience) ማሰባሰብ፣ መመዝገብ እና መዘከር ሲሆን ይህም የተረፉት ሰዎች ከእነዚህ ገጠመኞች ከደረሰባቸው የስሜት ቀውስ (trauma) መዳን እንዲጀምሩ ነው።

እ.ኤ.አ. በ 2015 የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን የመጨረሻ ሪፖርቱን አውጥቶ 94 የተግባር ጥሪዎችን አሳትሟል ፣ ሁሉም የመንግስት እርከኖች በመኖሪያ ትምህርት ቤቶች የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ለመለወጥ የተቀናጀ ጥረት እንዲያደርጉ እና በእርቅ ሂደት ወደፊት እንዲቀጥሉ አሳስቧል።

የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን (TRC) ስራ በተለይ አስቸጋሪ የሆነውን የካናዳ ታሪክ ክፍል መመዝገብ ብቻ ሳይሆን ስለ የአገሬው ተወላጅ እና ተወላጅ ያልሆኑ ታሪክ እውነትን መናገሩ የተሻለ መጻኢ ለመገንባት የተሻለ መነሻ ነጥብ ይሰጠናል ከሚል እምነት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም የአዲሱ ዓይነት ተስፋ መጀመሪያ ነው።

ብዙ ፍረጃዎች (stereotypes) እና ችግሮች የሚከሰቱት ሰዎች ስለ የአገሬው ተወላጅ እውነቱን ወይም ማንኛውንም መረጃ ባለማወቅ ነው። መረጃውን እንዲፈልጉ እናበረታታዎታለን፣ የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽንን "የድርጊት ጥሪዎች" የሚለውን ያንብቡ፣ የጓደኝነት ማእከልን (Friendship Centre) ይጎብኙ ፡ የአገሬው ተወላጅ ደራሲያን መጽሃፎችን ያንብቡ፡ በአገር-በቀል አርቲስቶች የተፈጠሩ ጥበቦችን ይዳስሱ፡ ስለአገሬው ተወላጆች ትምህርት ይውሰዱ፡ ስለ የአገሬው ተወላጅ ጉዳዮች ለመነጋገር በስራ ቡድንዎ ውስጥ ቡድን ይመስርቱ፡ በመላው ካናዳ ውስጥ እንደ የእርቅ ጉዞ (Walk for Reconciliation) እና የብሔራዊ የአገሬው ተወላጆች ቀን (National Indigenous Day) እንቅስቃሴዎች ባሉ ዝግጅቶች ላይ ይሳተፉ።

ሁሉም ሰው የሚከበርበት እና የሚካተትበት ቦታ ለመፍጠር አንድ ላይ መስራት እና እርስ በርሳችን መደጋገፍ ያስፈልገናል። እርቅ በጣም ግላዊ ጉዞ እና ሁሉም ካናዳውያን የበኩላቸውን ሚና መጫወት ያለባቸው ነው።

ይህ መመሪያ በኮሪ ዊልሰን (Kory Wilson) ለISSofBC የተፈጠረ ወደ ካናዳ እንኳን በደህና መጡ ቪዲዮውን ለማጀብ ነው። ይህ መመሪያ እንደሌላ ካልተጠቀሰ የCC BY NC 4.0 License ፈቃድ አለው። ይህ ፍቃድ እንዲቀላቅሉ (remix)፣ እንዲያስተካክሉ (tweak) እና ከንግድ ውጪ በዚህ ስራ ላይ እንዲገነቡ ያስችልዎታል። አዲሶቹ ስራዎችዎ ለኮሪ ዊልሰን እውቅና እንዲሰጡና እና ንግድ ነክ ያልሆኑ መሆን አለባቸው። እባክዎ የሚከተለውን መግለጫ ለባለቤትነት ይጠቀሙ፡ እንኳን ወደ ካናዳ የጥናት መመሪያ በደህና መጡ በኮሪ ዊልሰን (Kory Wilson)፣ በCreative Commons Attribution-Noncommercial license ©2019, Kory Wilson ይገኛል።